# ትግሉን የማስቀጠሉ ምትሀት

በባሕርዳር እየተካሄደ ያለው የሦስት ቀን የስራ ማቆም አድማ ዛሬ የመጨረሻው ነው። ይህ ማለት አንባገነኑ መንግስት መልስ እስካለሰጠ ትግሉ ይቆማል እንዳይደለ የታወቀ ነው። ለሁሉም ሁለት ተውኔቶች ሕወሐት ይዛልን ቀርባለች። አንደኛው መጋገሯቿን ሰብስባ ጋዜጣዊ መግለጫ አውጥታለች። የስብሰባ ውጤት ሆኖ የተላለፈውን የሕወሐት (ወያኔ ትግራይ) መግለጫ ሲነበብ ለሌላ ዙር ውጊያና ፍጅት መዘጋጀቷን ያስገነዝበናል እናም እንዲህ ብሎ ሰፍሯል።

የአስተዳደር ጉድለት አለ ብሎ ማመኑን እና ህዝቡ ሰላማዊ በሆነ መልክ ጥያቄውን ይዞ መውጣቱን ብንገነዘብም ይልና ጥያቄውን የሚያራግቡት “ትምክህተኞች” እና “ጠባቦች” ናቸው ይላል። ይህ እርስ በርሱ የሚጋጭ መግለጫ ለአገር ውስጥ ፍጆታው “አሉ” ለመባል እና ትንሽም ቢሆን ደካሞችን ለመሳብ የተዘየደ መላ ሲሆን። ሁለተኛው አገሪቱ ህግ እና ደንብ በህገመንግስት ያጸደቀች እና የምትተዳደርም በዚሁ ተንተርሳ ስለሆነ።

ዜጎች በሰላማዊ መንገድ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። ይህ ህገመንግስታዊ መብትን ለመጠቀም ግን ፍቃድ ማገኘዋም ሰው ለሰላማዊ ሰልፍም ሆነ ጥያቄ ለማቅረብ የመንግስት ፈቃድ ማውጣት ይኖርበታል ይሉናል። በጀ። ፈቃዱን የሚሰጡት እነርሱ ከሆኑ ከአንባ ገነኖች በተገኘ ፈቃድ ግን አገር እና ሕዝብ ነጻ ሊሆን አይችልም። ሌላው “ትምክህተኞች” የሚሉት አማራውን ዜጋ ሲሆን “ጠባብ” የሚሉት ደግሞ ኦሮሞውን እንደሆነ ግልጽ ነው።

ሕወሐት 25 አመታት በስልጣን ላይ ለመቆየት ያስቻላት አቅም ኖሯት ሳይሆን የኢትዮጵያውያኑን የቋንቋ እና ጥቃቅን ልዩነቶችን በመጠቀም ብሎም እነዚያ የሕዝብ ጸጋ ናቸው የምንለውን በሽህወች አመታት አብሮነታችን ድክመትን ሳይሆን ጥንካሬን፣ ልዩነትን ሳይሆን አንድነታችንን ያጠናከሩልንን ማንነት ለሰይጣናውዊ አላማው በመገልገሉ ነው።

ሕወሀት ስልጣን ከያዘች ጀምሮ ከአርባ ጉጉ እስከትናንትናው የባህርዳር ፍጅት ዜጎችን በእጅ አዙርም ሆነ በቀጥታ ገዳይ እርሷው ናት። ይህች አናሳ ቡድን በስልጣን መቀጠል፣ ማዘዝና ህገወጥ መሆን የሚያስችላት በያካባቢው በምትከፍላቸው መጋገሮች በመገልገሏ ነው።

እርስ በእርስ ማባላት በተለይም በአማራ እና በኦሮሞ መካከል ቁርሾ ፈጥራ ያንን ማስቀጠል ፍቱን መድህኒቷ ነው። እናም አዲስ ቧልት ሰሞኑን ይዛ ልትመጣ ይጠበቃል። የአገር ነጻነት ከተመለሰ በኋላ በህዝብ ሰላምን፣ ዴሞክራሲን እና አንድነትን ሊያስቀጥሉ የሚችሉ የጋራ ስምምነቶችን ለእርሷ በሚበጅ እና ስምምነት እንዳያመጣ ዘይዳ ልትጠቀምበት ትችላለች። ለዚህ ተጠንቅቆ መጠበቅ የእኛ ተግባር ነው።

አሁንም የህዝብ ጥያቄ መሆን እና መቀጠል ያለበት ይህች አንባገነን መወገድ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻ ምርጫ እንዲኖረው

ለፖለቲካ እና ሲቪል ድርጅቶች ነጻነት መስጠት በአስቸኳይ የሽግግር ስርአት እንዲመሰረት መጠየቅ። ይህች ዘረኛ ቡድን ያለምንም ቅድመሁኔታ ስልጣን እንድታስረክብ ነው መሆን ያለበት። የስምምነት መንግስት አስፈላጊ መሆኑን መጠራጠር የለብንም።
ሕወሐት እና በስሯ የተኮለኮሉ ድርጅቶች ግዜው መምሸቱን እናም ለ 25 አመታት የዘረፉትን ለመሰብሰብ እንኳን የሚያስችል ሁኔታ አለመኖሩን ተረድተው ጨርሶ ሁሉም ነገር ከማብቃቱ በፊት የህዝብን ጥያቄ መቀበል፣ በእውነቱ ለህዝቡ ብቻ ሳይሆን በይበልጥ ጥቅሙ ለእነርሱ መሆኑን ሊያውቁት ይገባል።

በተለይ ይህችን ዘረኛ ቡድን እንደድሮው ታስጥለናለች ብሎ አምኖ እና ተማምኖ መቀመጡ ውርደት ያስከትልባቸዋል። ሲሆን አሁኑኑ ከሕዝብ ጎን መቆም እና ሲገድሉ፣ ሲያስገድሉት እና ሲያስሩት የኖሩትን ህዝብ መተባበሩ ትንሽም ቢሆን ህዝብ ይቅር ባይ ነው። ከወያኔ ጋር ቆሞ እስከመጨረሻ መገኘቱ አጓጉል ውርደት ማስከተሉ አይቀሬ ነው።

በአማራ ክልልም ሆነ በኦሮሚያ ክልሎች ውስጥ በጸጥታ አስከባሪነት የሚሰሩ የስርአቱ አገልጋዮች በዚህ በሚፈሰው ደም የቀጥታ ተሳታፊ በመሆናቸው ወንጀሉ ከአገር እና ሕዝብ ክህደት ጋር ይየያዛል። ወያኔዋ የማታ ማታ እነዚህን ጉዶቿን ተሸክማ አትቀጥልም እንዴውም እነርሱን ወንጀለኛ አድርጋ የእርሷን ንጽህና ለማሳየት የምትጠቀምበት ሁኔታ እንደሚመጣ መጠራጠር አይገባም።

ሌላው የክልል የጸጥታ ሀይል ሆነው ለዚህ ስርአት የሚያገለግሉ፣ በደህንነት ስር ሕዝባቸውን የሚሰልሉ እና ለወንጀለኛዋ ቡድን አሳልፈው የሚሰጡ ሁሉ እራሳቸውን ከደሙ ንጹህ አድርገው ከሕዝብ ጎን ቢቆሙ መቻውንም ሕዝብ ይቅር ባይ ነው እና የሰሩትን ብዙ ጉዳይ ሳይሆን ትንሽም ብትሆኑ ከጎኑ ቆመው ያበረከቱትን ትብብር ስለማይ ይቅርታው ሰፊ ይሆናል። ጎበዝ ሳይመሽ በግዜ ጥግ ያዙ ልንል ይገባል። ወያኔ ብቻዋን ባለእዳነቷን ትረከብ።

ሌላው በትናንቱ አዲስ ነገር እንደሰማነው ከሕወሐት ሰፈር የሚሸት ነገር እንዳለ ይገመታል። ይህም የኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄን መለስሁ፣ በተጨማሪም ይህን እና ያንን አደርጋለሁ ብላ ብቅ ልትል ብሎም የህዝብ ክፍፍልን በአዲስ መልክ ማስቀጠል እችላለሁ ብላ ልታስብ ትችላለች። መላው ግን የእርሷን ስልጣን የማስቀጠል ስለሆነ ዜጋ ጀሮን አቃንቶ ማዳመጥ እና የፋሽስትን ቧልት ማፍረስ ይጠበቅብናል።
የሰማእታትን ቤተሰቦች አስመልክቶ

በባህርዳር፣ በጎንደር፣ ደብረ ማርቆስ፣ በመላ ኦሮሚያ እየተካሄደ ባለው ሕዝባዊ ትግል ከፍተኛ መስዋ'እትነት ተከፍሏል። መስዋ'እትነቱም ያበቃለት ሳይሆን ቀጣይ ስለሆነ ከወዲሁ ሊታሰብበት ይገባል። ወገን ለወገን መድረስ የታሰበውን ሕዝባዊ ትግል ግብ እንዲመታ ያደርጋል። ወያኔዋ ይህንም ልትጠቀምበት እያሰበች መሆኑን ከምታወጣቸው መግለጫወች እናያለን። የሆነው ሆኖ የእኛን ድርሻ መወጣቱ ለሕዝባዊው ትግል ግብ መምታት አስተማማኝ ይሆናል።

ለዚህ እንደምሳሌ መወሰድ ያለበት በፍልስጤም የነጻነት ትግል ውስጥ ለአመታት የታየው አንድ እናት እና አባት ልጃቸውን ሲያጣ ወይንም ቤት ንብረቱ በጠላት ሲፈርስ የሚደረግላቸው ትብብር ነው። ለምሳሌ ቤት ፈርሶ በሚቀጥለው ቀን ቤቱ ሙሉውን ይሰራል። እና ትግሉ ቀጣይ እንደሆነ ሁሉ ፍልስጤማውያን እኔ ብሞት እናት አባቴን ማን ይጦራል ብለው እንዳያስቡ ሕዝቡ ለዚህ ዋስትና መሆኑን በረጅሙ ትግላቸው አሳይተዋል።

እናም ለአላማ መሞት ሕይወት ነው እንዲሉም ሆኗል። ወደእኛ አገር ስንመጣ ለአለፉት 40 አመታት እናት ልጁን ተነጥቃ ያለጧሪና ጠያቂ ስትቀር ነው የታየው እናም ለህዝብ ትግል መሞት ትርፉ የበለጠ ጉዳት ብሎ ሁሉም እንዲያስብ ሆኗል። ይህን መቀየር ካልቻልን ለትግል ተሰልፎ መሞትን የሚቀበል ልናገኝ አንችልም። ስለሆነ ከዚህ መጀመር እንዳለበት መታሰብ ይኖርበታል።

የአንድ ሰሞን ወግ መሆንም የለበትም። ቋሚነት እና ዘላቂነት ያለው አዲስ ባህል ብንጀምር ታጋይ ሞልቶ ተርፎ ነው። ይህ መታሰብ ብቻ ሳይሆን ለሰማእታቱ ቤተሰቦች አንድ ነገር መጀመር ለነገ የሚተላለፍ አይደለም።

ድል ለኢጥዮጵያ ሕዝብ !!!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !!!

መንግስቱ ሙሴ

**http://www.ethiopanorama.com**